የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

2ኛ ዓመት ቁጥር 4 ሠመራ የካቲት 27 ቀን 1996 ዓ.ም	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት	2nd Year No. 4 Samara 6th, 2004

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት

አዋጅ ---------- ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 23/1996 ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት የተሻሻለው የኢንቨስትመንት አዋጅ

የአፋርን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠንና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል ኢንቨስትመንትን ማበረታታትና ማስፋፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የክልሉን ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማጠናከር የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች ተሳትፎ ማስፋፋትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያለውን የኢንቨስትመንት ህግ በተሻሻለ ህግ መተካቱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 2 /ለ/ ለክልል መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 23/1996 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

የተሻሻለው የ 1996 ዓ.ም የኢንቨስትመንት አዋጅ ስለመጽደቁ

የፀደቀው የክልሉ ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 5/1991 ዓ.ም ድንጋጌዎች ተሸረው የተሻሻለው የአፋር ክልል ኢንቨስትመንት አዋጅ በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

አንቀጽ 3

ትርጉም

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. «ኢንቨስትመንት» ማለት አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ወይም ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው።
2. «ማስፋፋት ወይም ማሻሻል» ማለት የነባር ድርጅትን የሙሉ አቅም ምርት ወይም አገልግሎት ከ 25% በላይ በእሴት ማሳደግ ሲሆን ይህም በዓይነት ወይም በመጠን ወይም በሁለቱም መጨመርን የሚያጠቃልል ነው።
3. «ድርጅት» ማለት ለትርፍ ሲባል የተቋቋመ ድርጅት ነው።
4. «ካፒታል» ማለት የሚተላለፍ ሰነድ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ ህንፃ ማደሻ የሥራ ማስኪጃ መብት የፖቴንት መብት ወይም ሌላ የንግድ ሃብት ነው።
5. «ሰው» ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው።
6. «ባለሃብት» ማለት በክልሉ ኢንቨስትመንት ያደረገ ባለሀብት ነው ወይም እንደቃሉ አገባብ ለአገር ውስጥ ባለሃብት እና ለውጭ ባለሃብት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ /5፣6/ እና በአዋጅ ቁጥር 375/1996/ እንደተሻሻለ የተሰጠውን ትርጉም ይሰጣል።
7. «ክልል» ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ነው።
8. «ጽህፈት ቤት» ማለት የኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት ማለት ነው።
9. «የኢንቨስትመንት ኮሚቴ ወይም አካል» ማለት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት ቦርድ፣ የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ወይም የዞንና የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ነው።
10. «ቦርድ» ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተመለከተው አካል ነው።
11. «የሚመለከተው አካል ወይም አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት» ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም የአፋር ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ማለት ነው።

አንቀጽ 4

የተፈፃሚነት ወሰን

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በማዕድንና ነዳጅ ፍለጋ መርመራና ማምረት ሥራዎች በሚደረግ ኢንቨስትመንት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

ክፍል ሁለት

ስለ ኢንቨስትመንት ዓላማዎች

አንቀጽ 5

ስለ ኢንቨስትመንት ዓላማዎች

በዚህ አዋጅ መሠረት አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት ወይም የኢንቨስትመንት አካላት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

ሀ/ የክልሉን ማህበረዊ አገልግሎት የማሟልበትና የኢኮኖሚ እድገቱን ማበረታታት

ለ/ የክልሉ ህብረተሰብ በምግብ ራሱን እንዲችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አስፈላጊ ሁኔታዎች ማመቻቸትና ማጠናከር።

ሐ/ የክልሉን ህብረተሰብ በተለይም ግብርና ኢንዱስትሪ እንዲሁም የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ማበረታታት

መ/ የክልሉን ሰፊ የተፈጥሮ ኃብት ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማልማት ኢንቨስተሮችን ማበረታታት

ሠ/ የክልሉን የገቢ ምንጭ ማሳደግ

ረ/ ወደ ውጭ የሚላኩ የክልሉ ምርቶች መጠን በጥራትና በዓይነት እንዲያድግ ማበረታታት

ሰ/ የክልሉን ኃብረተሰብ ሰፊ የሥራ እድል መክፈት

ሸ/ የውጭ ኢንቨስትመንት በክልሉ የኢኮኖሚ ልማት ተገቢውን ሚና እንዲኖረው ማድረግ

ክፍል ሶስት

የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት

አንቀጽ 6

የኢንቨስትመንት አካላት

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት እንደገና በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኢንቨስትመንት አካላት የሚከተሉትን ክፍሎች ያካትታል።

ሀ/ ቦርድ

ለ/ የክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

ሐ/ የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ

መ/ የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቶ

ንዑስ ክፍል አንድ

ስለ ኢንቨስትመንት ቦርድ

አንቀጽ 6

ስለ ኢንቨስትመንት ቦርድ መቋቋም

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት ቦርድ የራሱ ጽ/ቤት ሲኖረው የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት ከቦርድ ስልጣንና ተግባር ጋር በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናል።

2. የኢንቨስትመንት ቦርድ የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ሥራና ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ የሚወሰን ቁጥር ያላቸው አባላት ይኖሩታል።
3. የቦርዱ አባላት ከመንግስትና ከግሉ ሴክተር የተውጣጡ ይሆናሉ።
4. ቦርዱ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት አባላቶች ሲኖሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የን/ኢ/ት/ከ/ል/ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ የአባላቶቹን ብዛት ለመቀነስም ሆነ ለመጨመር ይችላል።

ሀ/ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ስራና ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ሲሆን ቢሮ ኃላፊው የቦርዱ ሰብሳቢ ይሆናል።

ለ/ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ኃላፊ ፀሐፊና ---------- አባል ይሆናል።

ሐ/ የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል

መ/ የአርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል

ሠ/ ንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል

ረ/ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል

ሰ/ የውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል

ሸ/ የእንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል

ቀ/ የመስኖ ልማትና መጠጥ ውሃ ኮንስትራክሽን ባለ ስልጣን ----- አባል

በ/ ባቱማ ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል

አንቀጽ 8

ስለቦርዱ ስብሰባዎች

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባሊያደርግ ይችላል።
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በቦርድ ስብሰባ ላይ ከተገኘ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

አንቀጽ 9

የቦር ስልጣንና ተግባር

1. የዚህን አዋጅ አፈፃፀምና የኢንቨስትመንት ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል ይመራል።
2. በኢንቨስትመንት ፖሊሲው ላይ ለሚነሱ ጉዳዮች ውሳኔ ይሰጣል።
3. ይህንን አዋጅ መሠረት ያደረገ ደንብ ለማውጣትና ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ያወጣል።
4. በኢንቨስትመንት ፈቃድና ከማበረታቻዎች አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በሚቀርቡት የይግባኝ አቤቱታ ላይ ውሳኔ ይሰጣል።
5. ጽ/ቤቱ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለውን ክፍያ ይወሰናል።
6. የጽ/ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅርና ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያ ያፀድቃል።
7. በየጊዜው የሚያወጣውን መመሪያ ኢንቨስተሮች በግልጽ እንዲያውቁት ያደርጋል።

8. የክልሉን ኢንቨስትመንት ለማበረታታት አስፈላጊ መመሪያዎች ያወጣል።
9. የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ሥራን ሊያበረታቱ የሚችሉ ደንቦችን እንደአስፈላጊነቱ እንዲሻሻልና እንዲወጣ ለክልሉ መንግስት መስተዳድር ም/ቤት ቀርቦ እንዲፀድቅ ለክልሉ መንግስት ም/ቤት ቀርቦ እንዲፀድቅ ለክልሉ መንግስት ም/ቤት የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀርባል።
10. የዞን የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ያቋቁማል ያደራጃል ይቆጣጠራል ይከታተላል።
11. የአዋጁን አፈፃፀምና ተጓዳኝ ጉዳዮችን ይወስናል ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል።
12. ለተፈቀደ የኢንቨስትመንት ኘሮጀክት የመሬት ጥያቄ የቀረበለት የክልል ቦርድ የፌዴራልና የክልሉን ኢንቨስትመንት አዋጅና የማበረታቻ ደንቡን መሰረት በማድረግ ጥያቄው በቀረበለት በ 30 ቀን ውስጥ የተጠየቀውን መሬት በኢንቨስትመነት ጽ/ቤት አካላት በኩል ለባለሀብቱ ያስረክባል።
13. ይህንን አዋጅና ሌሎች ደንቦችን መሠረት በማድረግ በቦርድ የተላለፉ ውሳኔዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በኮሚቶው ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል።

ንዑስ ክፍል ሁለት

ስለኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

አንቀጽ 10

የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

1. የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው መ/ቤት ሆኖ ተጠሪነቱ ለአፋር ብ/ክ/መንግስት ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ሲሆን የጽ/ቤቱ ኃላፊ በክልሉ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት ይሾማል።
2. የጽ/ቤቱ ኃላፊና ባለሙያዎች፣ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ይኖሩታል።

አንቀጽ 11

የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ኃላፊ ስልጣን ተግባር

1. የዚህን አዋጅ አፈፃፀምና ተጓዳኝ ጉዳዮች ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል።
2. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 12 የተዘረዘሩት ሥራዎች በጽ/ቤቱ እንዲተገበሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ተግባራዊ መሆናቸውንም ያረጋግጣል።
3. የጽ/ቤቱን የሥራ ኘሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለክልል መንግስት መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።
4. ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል። በህጉ መሠረት ተፈላጊ የሆኑት ሰራተኞች እንዲቀጠሩ ያደርጋል።
5. የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለክልሉ ንግ/ኢ/ት/ሰ/ከ/ል/ማስ/ቢሮ እና ለቦርዱ ያቀርባል።

አንቀጽ 12

የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የክልሉን የኢንቨስትመንት ጉዳዮች ይመራል እንቅስቃሴውንም ያበረታታል ያስተባብራል ያስፋፋል።
2. ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሊወስዱ የሚገቡ የፖሊሲና የአፈፃፀም እርምጃዎችን ያመነጫል ለቦርድ ያቀርባል ሲፈቅድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።
3. የክልሉን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አዲስ መረጃዎች ይሰበስባል ያገናኛል ይተነትናል ያሰራጫል ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶችን ያስተዋውቃል በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በኮንስትራክሽን፣ በመንገድና ትራንስፖርት
4. የክልሉን ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ይህንን አዋጅ ተደግፎ ለአፈፃፀሙ ደንብና መመሪያ በማዘጋጀት ደንቡ በክልሉ መንግስት መስተዳድር ም/ቤት ቀርቦ እንዲፀድቅ ለቦር ያቀርባል። የኢ.ፌ/ዲ/ሪ/መ/የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ደንብና መመሪያዎችን ያስፈጽማል።
5. ኢንቨስትመንት ለማበረታታት የሚጠቅሙ ኤግዚቪሽኖች፣ ስብሰባዎች፣ ስልጠናዎች ሴሚናሮች የመሳሰሉትን እንደ አግባቡ በክልሉ ያካሂዳል ለባለሃብቶች የምክር ድጋፍ ይሰጣል።
6. ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት በባለሀብቶችና በመንግስታዊ መ/ቤቶች በመስተዳድሮችና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።
7. ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚረዱ ጽሁፎችን መግለጫዎችን ፊልሞችንና የመሳሰሉትን በማዘጋጀትና በማሰራጨት የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል።
8. ከባለሀብቶች የሚቀርቡ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ማመልከቻ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም ከወጡት ደንቦችና መመያዎች አንፃር በመመርመር ለክልሉ ልማት ይጠቅማል ለሚለው የኢንቨስትመንት ፍቃድ በተጠየቀ በ 5 ቀናት ውስጥ ይሰጣል የማበረታቻ ጥያቄዎች ይወስናል።
9. የኢንቨስትመንት ፍቃድ የሰጣቸውን ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት ፍቃድ የያዛቸውን ግዴታዎችና ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል ፍቃዶችንም መዝግቦ ይይዛል።
10. በዞንና በወረዳ ሪፖርቶችን ያሰባስባል ለቦርድ ያቀርባል።
11. የጽ/ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ ይይዛል።
12. በኢንቨስትመንት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል ከነመፍትሄ ሀሳቡም ለቦርድ ያቀርባል።
13. ለክልሉና ለኃብረተሰቡ ጠቃሚ ያልሆኑትን የኢንቨስትመንት ማመልከቻ ጥያቄም ይከላከላል ይቆጣጠራል።
14. በክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ መሬት እንዲሰጣቸው ለተፈቀዱ ኘሮጀክቶች መሬት ይሰጣል።
15. ሌሎች ከበላይ አካላት የሚሰጡትን ተመሳሳይ ተግባሮችን ያከናውናል።

አንቀጽ 13

የገቢ ምንጭ

ጽ/ቤቱ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል

1. ክልል ም/ቤት በበጀት መደብ የሚሰጠው ገንዘብ
2. ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ
3. ከማንኛውም ሌላ ምንጭ የሚገኝ ገቢ እርዳታና ስጦታ

አንቀጽ 14

የሂሳብ መዛግብት

1. የጽ/ቤቱ ተገቢ የሆነ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶችን ይጠብቃል።
2. የጽ/ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በክልሉ ዋና ኦዲተር ይመረመራሉ።

ንዑስ ክፍል ሶስት

ስለ ዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ስለማቋቋም

አንቀጽ 15

የዞን ኢንቨስመንት ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በዚህ አዋጅ መሠረት የኢንቨስትመንት ኮሚቴ በዞን ደረጃ ይቋቋማል።
2. የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሲሆን የዞን ም/ቤት መስተዳድር ለኢንቨስትመንት ኮሚቴ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

አንቀጽ 16

የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ አባላት

1. የዞን መስተዳድር ዋና አስተዳዳሪ ---------- ሰብሳቢ
2. የዞን ኢንቨስትመንት ዴስክ ---------- ፀሐፊና አባል
3. የዞን ንግድ ኢ/ት/ከ/ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ---------- አባል
4. የዞን አርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ---------- አባል
5. የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ---------- አባል
6. እንስሳትና እርሻ ልማት ዴስክ ---------- አባል
7. ንግድ ኢ/ት/ዴስክ ---------- አባል
8. ሥራና ከተማ ልማት ዴስክ ---------- አባል

አንቀጽ 17

የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

1. የኢንቨስትመንት አዋጅ በሚደነግገው መሠረት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችና ተግባራዊነታቸውን በቅርብ ይቆጣጠራል ለባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።
2. በሥሩ የሚገኙትን ወረዳዎች የኢንቨስትመንት ሪፖርት ያጠናቅራል ለጽ/ቤቱና ለቦርድ ያቀርባል።
3. በቦርድና በክልሉ ኢንቨስትመነት ጽ/ቤት የተላለፉትን የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎች መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ለኢንቨስትመነት ተግባር የሚውል መሬት በመመደብና የመደቧቸውን መሬት የሚመለከት መረጃዎችን ለኢንቨስትመንት ቦርድ ያስተላልፋል።

ንዑስ ክፍል አራት

ስለወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ መቋቋም

አንቀጽ 18

የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ መቋቋም

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት ኮሚቴ በወረዳ ደረጃ ይቋቋማል
2. የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ሲሆን የወረዳ መስተዳድር ም/ቤት ለኢንቨስትመንት ኮሚቴ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

አንቀጽ 19

የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ አባላት

1. የወረዳ መስተዳድር ም/ቤት አስተዳዳሪ ---------- ሰብሳቢ
2. የወረዳ አርብቶ አደር ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ---------- አባል
3. የወረዳ እንስሳት እርሻ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ---------- አባል
4. የወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ---------- አባል

አንቀጽ 20

የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ስልጣንና ኃላፊነት

1. በኢንቨስትመንት አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ተግባራዊነት ይቆጣጠራል ለኢንቨስትመንት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።
2. ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ክፍሎችንና ለልማት የሚውሉ አካባቢዎችን ይከልላል ጥናት ያካሂዳል የተከለሉ ሥፍራዎችን በስፋትና በመጠን ለይቶ ለዞን ኮሚቴ ያቀርባል።
3. ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ የወረዳውን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል።
4. የኢንቨስትመነት እንቅስቃሴን በተመለከተ አስተማማኝ መረጃዎችን ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቶ ያቀርባል።
5. ከሚመለከታቸው አካል ስለኢንቨስትመንት የሚሰጡትን መመያዋችና ውሳኔዎች ያስፈጽማል።
6. የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 21

የዞንና የወረዳ ኢንቨስትመነት ኮሚቴ ስብሰባዎች

1. የዞንና የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቶ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል።
2. አብዛኛው የኮሚቴ አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ተቆጥሮ ስብሰባውን ማካሄድ ይችላሉ።
3. ማንኛውም ስብሰባ ላይ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ መሰረት ይሆናል ድምጽ እኩል በእኩል ከሆነ ሊቀመንበሩ ሰብሳቢው ወሳኝ የሆነ አብላጫ ድምጽ ይኖረዋል።
4. ኮሚቴው በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ላይ አማካሪዎች ያለድምጽ እንዲገኙ ሊያደርግ ይችላል።

ክፍል አራት

ስለ ኢንቨስትመንት ፈቃድ

አንቀጽ 22

ለኢንቨስትመንት ፍቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የኢንቨስትመነት ፍቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ባለሀብት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር በአንድ ቅጅ (ኮፒ) አግባብ ላለው ለኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ማቅረብ አለበት።

ሀ/ ማመልከቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ስልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ፎቶ ኮፒ

ለ/ ኢንቨስትመንቱ የማካሄደው በግለሰብ ከሆነ የባለሃብቱ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ እና ሁለት የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶ ግራፎች

ሐ/ ኢንቨስትመንቱ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ወይም ማህበሩ አዲስ የሚቋቋም ከሆነ ከዚህ በተጨማሪ የማህበርተኞቹ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሃብትነት ሰርትፊኬት ፎቶ ኮፒ

መ/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በመንግስት የልማት ድርጅት ከሆነ ድርጅቱ የተቋቋመበት ደንብ ፎቶ ኮፒ ወይም የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ እና

ሠ/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በህብረት ሥራ ማህበር ከሆነ የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ

ረ/ ስለኢንቨስትመነት ኘሮጀክት መግለጫ

ሰ/ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ የሚፈልጉትን መሳሪያዎችና እቃዎች አይነትና ብዛት የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ፣

ሸ/ የውጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች ሲኖሩ ለተተኪ ኢትዮጵያውያን ስለሚሰጠው የስልጠና ኘሮግራምና ስለሚተኩት የጊዜ ገደብ መግለጫ፣

ቀ/ እንደኘሮጀክቱ ልዩ ፀባይ አግባብ ያላቸው ሌሎች መረጃዎች፣

አንቀጽ 23

ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል ስለሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ማመልከቻ

ማንኛውም ባለሀብት የማስፋፋት ወይም የማሻሻል የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀዉን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ማቅረብ አለበት።

ሀ/ የማመልከቻ ቅጹ የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ስልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ፎቶ ኮፒ፣

ለ/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ እና

ሐ/ የነባር ድርጅቱ የፀና የንግድ ሥራ ፍቃድ ፎቶ ኮፒ

አንቀጽ 24

ስለኢንቨስትመንት ፍቃድ አሰጣጥ

1. አግባባ ያለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት የኢንቨስትመነት ፍቃድ ማመልከቻው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 እና 23 መሠረት ተሟልቶ ከቀረበለት በባለሀብቱ ሊካሄድ የታቀደውን የኢንቨስትመነት ሥራ ከዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም ከሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አንፃር በመመርመር በ 5 የሥራ ቀናቶች ውስጥ

   ሀ/ ማመልከቻውን ከተቀበለው ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ይሰጣል ወይም

ለ/ ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለሀብቱ በጽሁፍ ያሳውቃል።

2. አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት የኢንቨስትመንት ፍቃዱን ከሰጠ በኋላ ለአስፈላጊው ክትትል ለሚመለከታቸው የሴክተር መ/ቤቶች በደብዳቤ ያሳውቃል።
3. የኢንቨስትመንት ፍቃድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

   ሀ/ የባለሀብቱን ስምና ዜግነት፣

   ለ/ የኢንቨስትመንቱ የሥራ መስክ፣

   ሐ/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄድበትን አካባቢ ወይም መስተዳድር፣

   መ/ የኢንቨስትመንቱ ካፒታል መጠንና አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ያስፈልጋሉ ሎ ያመነባቸውን ሌሎች ዝርዝሮች
4. የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰጠው ባለሀብት የኢንቨስትመንት ኘሮጀክትን ግንባታ አጠናቆ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ የንግድ ወይም የሥራ ፍቃድ እንዲያወጣ አይጠየቅም።
5. አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ሳይሰጥበት የኢንቨስትመንትን ፍቃድ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ አይቻልም።
6. የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለሌላ ሰው ሲተላለፍ ወይም በይዘቱ ላይ ሌሎች ለውጦች ሲያጋጥሙ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት አካል ቀርቦ መሻሻል አለበት።

አንቀጽ 25

የኢንቨስትመንት ፍቃድ እድሳት

1. የኢንቨስትመንት ፍቃድ ምርት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት እስከሚጀምርበት ድረስ በየዓመቱ መታደስ አለበት ሆኖም ባለሀብቱ ስለኢንቨስትመንቱ አፈፃፀም ሂደት በየሰድስት ወሩ አግባብ ላለው ኢንቨስትመንት አካል ሪፖርት ማቅረብ አለበት።
2. የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለማደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፍቃዱ የሚያገለግልበት የአንድ ዓመት ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት።
3. አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ባለሀብቱ የኘሮጀክት ግንባታውም ሊጀምር ወይም ሊጨርስ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ሲያምንበት ፍቃዱንም ያድሳል።

አንቀጽ 26

የኢንቨስትመነት ፍቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ

1. ባለሀብቱ የኢፌዴሪ ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 እና አዋጅ ቁጥር 375/1996 እንደተሻሻለ ወይም የክልሉን ኢንቨስትመንት አዋጅና እነዚህን አዋጆች ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችን ወይም መመያዎችን የጣሱ እንደሆነ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እስኪወሰድ ድረስ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል የኢንቨስትመንት ፍቃዱን ሊያግድበት ይችላል።
2. አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ በተጨባጭ ሲያረጋግጥ የኢንቨስትመንት ፍቃዱን ሊሰርዝ ይችላል።

   ሀ/ ባለሀብቱ የኢንባስትመንት ፍቃዱን ያገኘው በማታለል ወይም በሀሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፣

ለ/ ባለሀብቱ ከህግ ውጭ የኢንቨስትመንት ፍቃዱን ለሌላ ሰው ካስተላለፈ፣

ሐ/ ባለሀብቱ ያለበቂ ምክንያት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 በተደነገገው መሠረት የኢንቨስትመንት ፍቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ፣

መ/ የተሰጡ ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጭ ውለው ወይም ከህግ ውጭ ለሌላ ሰው ተላልፈው ከተገኙ፣

ሠ/ ባለሀብቱ የንግድ ሥራ ፍቃድ ሳያወጣ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ እንደሆነ፣

3. ከሚመለከተው አካል የፍቃድ እገዳ ወይም ስረዛ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ምክንያቱ ለባለሀብቱ በጽሁፍ መገለጽ አለበት ባለሀብቱም አስተያየቱን እንዲያቀርብ የአንድ ወር ጊዜ ይሰጠዋል።
4. ባለሀብቱ አስተያየቱን ካልሰጠ ወይም የሰጠው አስተያየት በሚመለከተው አካል ታይቶ አጥጋቢ ካልሆነ ፍቃድ የማገድ ወይም የመሰረዝ እርምጃ ይወሰዳል።
5. የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰረዘበት ባለሃብት ፍቃድ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ሲያገኝ የነበረው ጥቅም ይቋረጥበታል።
6. ፍቃዱ የተሰረዘበት ባለሃብት በማበረታቻነት ያገኘውን ጥቅሞች ማለትም ከቀረጥ ነፃ ያስገባቸውን የግንባታም ሆነ የማምረቻ መሳሪያወች ፍቃድ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ያደርጋል።
7. የኢንቨስትመንት ፍቃድ ከሰው የክልሉ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ወይም በፍ/ቤት ውሳኔና ትዕዛዝ በስተቀር በሌላ በማናቸውም አካል ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ አይችልም።

አንቀጽ 27

የኢንቨስትመነት ፍቃድ ስለጠፋበት ወይም ስለተበላሸበት ባለሀብት

ፍቃድ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት መሆኑን በማስረጃ በማስደገፍና በማረጋገጥ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት ወይም የኢንቨስትመንት አካላት ወይም ፍቃዱ ለተመዘገበበት ጽ/ቤት በማመልከት ምትክ ወይም አዲስ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል። ሆኖም፡-

ሀ/ የጋዜጣ ማስታወቂያ በአመልካቹ ወጪ መውጣት አለበት።

ለ/ በ 1 ወር ጊዜ ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ የደንቡን ክፍያ ከከፈለ በኋላ ምትትክ ፍቃድ ይሰጠዋል።

ሐ/ የተበላሸ ፍቃድ ለጽ/ቤቱ ሊመልስ ይገባል።

አንቀጽ 28

ስለ አቤቱታ አቀራረብ

1. በኢንቨስትመነት ፍቃድ በማበረታቻዎች ጥያቄ ላይ አግባብ የለው የኢንቨስትመንት አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ባለሃብት ውሳኔው በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለኢንቨስትመንት ቦርድ እንደአግባቡ ለክልል መስተዳድር አካል ማቅረብ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት ቅሬታ የቀረበለት የኢንቨስትመንት ቦርድ ወይም የክልል መስተዳድር አካል በ 15 ቀን ውስጥ ቅሬታውን አይቶ ውሳኔ መስጠት አለበት።

ክፍል አምስት

ስለኢንቨስትመንት ዋስትናና ጥበቃ

አንቀጽ 29

ስለኢንቨስትመንት ዋስትናና ጥበቃ

1. ለኢንቨስትመንት የዋለ ሀብት ለሕዝብ ጥቅም ሲባልና በህግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊወሰድ ወይም ሊወረስ አይችልም።
2. ለኢንቨስትመንት የዋለ ሀብት ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድ ወይም ሲወረስ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ሳይዘገይ መከፈል አለበት።

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 30

ስለካፒታል ገደቦች

በግል ባለሃብቶች ስለሚካሄዱ የሥራ መስኮች በመንግስት ስለሚካሄዱ የሥራ መስኮችና ስለቴክኖሎጂ ሽግግር ውሎች በሚመለከት በኢት/ፌዴ/ዲሞ/ሪፐ/ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 እና በአዋጅ ቁጥር 375/1996 እንደተሻሻለ ላይ የተደነገጉት በተመሳሳይ በዚህ አዋጅም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ 31

ስለማበረታቻዎች

1. በአዋጅ ቁጥር 280/1994 እና በአዋጅ ቁጥር 375/1996 እንደተሻሻለ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጽህፈት ቤቱ የክልሉን ኢንቨስትመንት ማበረታቻ በደንቡና መመሪያ መሠረት ለባለሀብቶች ያቀርባል።
2. ባለሀብቶች ከቀረጥ ነፃ ለክልሉ ከሚገቡ በገቢ እቃዎች ላይ ከሚጣል ታክስና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ የክልሉ የኢንቨስትመንት አካል ጥያቄውን በ 5 ቀናት ውስጥ መርምሮ ተገቢነቱን ሲያረጋግጥ ካስፈላጊው መረጃ ጋር ለገቢዎች ሚኒስቴር ያስተላልፋል።

አንቀጽ 32

ባለሀብቶችን በአንድ ማዕከል ስለማስተናገድ

1. የክልል ኢንቨስትመንት አካላት የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለሰጧቸው ባለሀብቶች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የሚከተሉትን አገልግሎቶች እንደአግባቡ የሚመለከታቸውን የክልል አስፈፃሚ አካላትን በመወከል ይሰጣሉ።
   ሀ/ የንግድ ምዝገባ መፈፀም
   ለ/ ለውጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች የሥራ ፍቃድ መስጠት
   ሐ/ ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ደረጃ መስጠት እና
   መ/ የንግድ ሥራ ፍቃድ መስጠት
2. የክልል ኢንቨስትመንት አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ተግባር የሚያከናውነው አግባብ ያላቸውን ሕጎች በመከተል ይሆናል።

3. አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ ሠ መሠረት የንግድ ሥራ ፍቃድ ማመልከቻ ሲቀርብለት ጉዳዩን አግባብ ካለው ሕግ አንፃር በመመርመር በ 5 የሥራ ቀን ውስጥ
   ሀ/ ማመልከቻውን ከተቀበለው ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል የንግድ ሥራ ፍቃዱን ይሰጣል ወይም
   ለ/ ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለሀብቱ በጽሑፍ ያሳውቃል።
4. በንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 ለአንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ሀ የተመለከተው ቢኖርም አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስራያ ቤት ባለሀብቱ አግባብነት ያለው የአገሪቱን ሕጐችና መመሪያዎች ጠብቆ ለመስራት ግዴታ እንዲገባ በማድረግ የንግድ ሥራ ፍቃድ ይሰጣል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የንግድ ሥራ ፍቃድ የሚሰጠው የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ቢሆን በመወከል ብቻ ይሆናል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ከተጠቀሱት ሰነዶች ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ማሻሻያዎች የማዋዋል የማደስ የመተካት ወይም የመሠረዝ ሥራ የሚከናወነው አግባብ ባላቸው የክልል አስፈፃሚ አካላት ነው።
7. አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን አገልግሎቶች ከሰጠ በኋላ ለአስፈላጊው ክትትል አግባብ ላለው የሴክተር መስሪያ ቤት በደብዳቤ ያሳውቃል።

አንቀጽ 33

ውሃ ስለማግኘትና ስለአጠቃቀሙ

1. ማናቸውም ባለሀብት ለኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ውሃ አጠቃቀም ከሚመለከተው የክልል መንግስት አካል ጋር በሚያደርገው ውል መሠረት ለማግኘት ይችላል።
2. ስለአጎራባች የውሃዎች ሀብት አጠቃቀም በሚመለከት የኢት/ፌ/ዲሞ/ሪፓ/መንግስት የውሃ ሀብት ልማት ሚኒስተር ባወጣው ሕግና ደንብ መሠረት ባለሀብቱ ለኢንቨስትመንቱ ውሃ ሊያገኝና ሊጠቀም ይችላል።

አንቀጽ 34

ስለማዕድን አጠቃቀም

1. ባለሀብቱ ለኢንቨስትመንቱ ስለሚጠቀምባቸው ማዕድናት የክልሉ ውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጅ ቢሮ በሚያወጣው ደንብ መመሪያ መሠረት ሊጠቀም ይችላል።
2. በማዕድን ክፍለ ኢካኖሚ ኢንቨስት ስለሚደረግበት ሁኔታና ማበረታቻ አፈቃቀድ የኢት/ፌ/ዴ/ሪፓ/መንግስት የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስተር ሕግ መሠረት በማድረግ እንዲሁም በክልሉ ውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ሕግ መሠረት ይወሰናል።

አንቀጽ 35

የኢንቨስትመንት መረጃዎችን ስለማስተላለፍና ስለመስጠት ግዴታ

1. ማናቸውም የክልል የኢንቨስትመንት አካል ስለክልሉ ሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እድል የተጠናከሩ መረጃዎችን የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል አስፈፃሚ አካል ኢንቨስትመንት ነክ መረጃዎችን አግቦብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ሲጠይቅ የመስጠት ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 36

አዋጁን የመተግበር ግዴታ

1. ማንኛውም የክልሉ ኢንቨስትመንት አካል ይህን አዋጅ የመተግበር ግዴታ አለበት።
2. በዚህ አዋጅ ስላላተገለፀው የኢንቨስትመንት ጉዳዮች የኢፌዴራ መንግስት ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 እና አዋጅ ቁጥር 375/1996 ኡራደጸሻሽለ ላይ የተደነገጉት በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 37

ደንብ የማውጣት ስልጣን

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንቨስትመንት አዋጅና የክልል ኢንቨስትመንት አዋጅን ሳይቃረን የክልሉ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣ ወይም ሊያሻሽል ይችላል።

አንቀጽ 38

የተሻሩ ሕጎች

1. የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 5/1991 እንደተሻሻለ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውንም ሕግ ደንብ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 39

የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ለተፈቀዱ ኢንቨስትመንቶች በአዋጅ ቁጥር 5/1991 እንደተሻሻለ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች መሠረት የሚሰጡ ማበረታቻዎች ተፈፃሚነት ይቀጥላሉ።
2. በአዋጅ ቁጥር 5/1991 እንደተሻሻለ መሠረት ማበረታቻ የሚያገኝ ባለሀብት በዚህ አዋጅና ይህንን በተሰጠው ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገ ይህንኑ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በማስታወቅ የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ይችላል።
3. ይህ አዋጅ በወጣጣበት የበጀት ዓመት በሕግ መሠረት የተሰጠ ወይም የታደሰ ፍቃድ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጠው ወይም እንደታደሰ ይቆጠራል ወይም ፍቃዱ ይህ አዋጅ በወጣበት እለት ፍቃድ በተሰጠበት ሕግ መሠረት ሊታደስ የሚችል ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ይታደሳል።

አንቀጽ 40

የኢንቨስትመንት አዋጁን ስለማሻሻል

በክልሉ ምክር ቤት አባላት አንድ ሶስተኛ ወይም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአብላጫ ድምጽ ውሳኔ የኢንቨስትመንት አዋጁ እንዲሻሻል የማሻሻያ ሀሳብ ወይም ጥያቄ ሲቀርብ የአዋጁ ድንጋጌዎች በክልሉ ምክር ቤት አባላት ሶስት አራተኛ ድምጽ ሊያሻሽሉት ይችላሉ።

አንቀጽ 41

አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት 27/1996 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል

ሠመራ

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብሐራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳደር